# <u>ታሪክ ስባስታሪኩ</u>

ከታደለ ኣብርሃም
29/06/2009 ዓ.ም

*"ታሪክን መማር ለሁሉ ሰው ይበጃል፤ የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅም የእውነተኛ ታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው፤ እውነተኛውን ታሪክ ለመጻፍም ቀላል ነገር ኣይደለም፤ የኣገራችን ታሪክ ፀሓፊዎች ግን በነዚህ ላይ ኃጢኣት ይሰራሉ፤ በትልቁ ነገር ፈንታ ትንሹን ይመለከታሉ፤ በእውነት መፍረድንም ትተው በኣድልዎ ልባቸውን ያጠብባሉ፤"*

*(ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ ኣጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ)*

ከሰሞኑ ኣንዳንድ የተዛቡ ታሪኮችን የሚዘግቡ ልዩ ልዩ ፅሑፎች በተለያዩ የሕትመትና ኤሌክትሮኒክ ሚድያዎች ተመለከትኩ፤ የኣክራሪዎች የሰሞኑ ትኩረት መሆኑንም ግንዛቤ ወሰድኩ ።

በመሠረቱ ግን ታሪክ ጠቃሚና ኣስተማሪ ሊሆን የሚችለው በትክክል፣ በእውነተኝነትና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሲጻፍ ነው፤ ኣንዳንድ ሰዎች ግን ትልቁን ስዕል በመተው በተለያዩ የተነጠሉ ድርጊቶች ላይ ብቻ በማተኮር ታሪካዊ ዕውነታዎችን በማምታታትና በማጨናበር ያልነበረ ታሪክ ለመጻፍ ይሞክራሉ፤ ትልቁን እንስሳ ዝሆን በጭራው ብቻ ለመግለጽ እንደመሞከር ማለት ነው፤ 'ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ' እንዲሉ የኣንዱን ጀግንነት ለሌላው፣ የሌላው መጥፎ ባሕርይ ደግሞ ለሌላኛው ለማሸከም ይሞክራሉ፤ ይኼ ኣካሄድ ኣዋቂዎች ንቀው የሚያልፉት ቢሆን እንኳ ብዙ ልምድ የሌላቸውን ወጣቶችን ግን የማወናበድ ኣቅም ኣለው፤ የፀሓፊዎቹም እኩይ ዓላማ ወጣቱን ትውልድ በማወናበድ ወዳልሆነ ተግባር መምራት ሊሆን ይችላል ።

ያየሁኣቸው ፅሑፎች የኣፄ ዮሓንስ ታሪክ የተመለከቱ ሲሆን፣ ፀሓፊዎቹ ንጉሠ ነገሥቱን በጣም በተሳሳተ መንገድ ሊገልጹኣቸው ሞክረዋል፤ በመሠረቱ ግን መማር ካለብን ከትክክለኛው ታሪክ እንጂ፣ የሞራልና የስነ ልቦና ውድቀት ያጋጠማቸው ግለሰቦች ከጻፉት ፅሑፍ መሆን የለበትም።

ስለ ነገሥታቱ ታሪክ ስናወራ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች፣ ማለትም፣

1. ሁሉም መሣፍንት ለሥልጣናቸው ቀናኢ መሆናቸውና ተቀናቃኞቻቸውን ለማሸነፍም የውጭ መንግሥታት ድጋፍ ይሹ እንደነበር፣
2. መሣፍንቱ፣ ከኛ ከተራ ሰዎቹ ይልቅ እርስ በራሳቸው ይቀራረቡ እንደነበርና ባምቻ ጋብቻ የተሳሰሩ እንደሆኑ፣ ልብ ማለት ይገባል፤

ኣፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ካለፉ በኋላ፣ እሳቸውን ተክቶ ንጉሠ-ነገሥት ለመሆን ሦስት ተቀናቃኝ ኃይሎች ብቅ ብለዋል፤ እነዚህም፣ የትግራዩ ደጃች ካሳ ምርጫ፣ የወሎው ዋግ ሹም ጎበዜ እና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ነበሩ።

የወሎው ዋግሹም ጎበዜ፣ ኣፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተሰኝተው ከሁሉም ቀድመው ራሳቸውን ንጉሠ-ነገሥት ብለው ያወጁ ሲሆን፣ ደጃች ካሳ እንዲገቡላቸው፣ የሰራዊታቸውን ብዛት ለማስረዳትና ነገሩ በዛቻ የሚከናወን መስሏቸው ኣንድ ስልቻ ሙሉ ጤፍ ኣስሞልተው "የሰራዊቴ ብዛት ይኼን ያክል ነው" ሲሉ ላኩባቸው ይባላል፤ ካሳም

*" ከቱርክ ይዋጋል እንኳን ካንካሳ*

*ያባ ፈንቅል ልጅ ወሬሳው ካሳ"*

ብለው ፎክረው ወዲያውም " ወታደርህ እንደዚህ ቢበዛ በጥይት ቆልቼ ነው የምሰደው" ሲሉ ጤፉን ቆልተው ላኩላቸው ይባላል፤ ይህ በኣፍ የተነገረ ታሪክ ወታደራዊ ልዩነታቸው በምን በምን እንደሆነ ያሳያል፤ ኣፄ ተክለ ጊዮርጊስ ለናፖሊዎን ሦስተኛ በጻፉትም ደብዳቤ ላይ

*" ይድረስ እግዜር መርጦ ካነገሠዎ ንጉሠ-ነገሥት ናፖሊዎን፣*

*..... እኔ የእርስዎን ወዳጅነት እጅግ እፈልጋለሁ፤ ኣፄ ቴዎድሮስ*

*ያከፉትን (ያበላሹትን) ነገር ሁሉ ከምክርዎና ከፍቅርዎ ጋር በእግዚአብሔር*

*ኃይል ኣቀናዋለሁ፤ ..... ደጃች ካሳን ሾሜ ኣገር ጠብቅ ብዬ ብተወው*

*ኣምጦ (ሸፍቶ) ኣልታዘዝም ኣለ ። ኣሁን ግን የምጠይቀው ነኝና ኣይፍረዱብኝ...."*

ይላሉ።

"የምጠይቀው ነኝና ኣይፍረዱብኝ" ሲሉ ሥጋታቸው ለመሸነፉ ሳይሆን የፈረንሳይም የእንግሊዝም መሪዎች፣ ካሳን ወግተው ካሸነፉ በኋላ 'ለምን ወጋኸው' ብለው እንዳይቀየሟቸው ነው፤ ባለቤታቸው እቴጌ ድንቅነሽ ግን የወንድማቸውን ልብ ያውቁ ስለነበረ ኣስቀድመው ቸኩለው ወደ ጦርነት እንዳይገቡ በሚከተለው ግጥም መከረዋቸው ነበር፤

| | |
|---|---|
| *"ኣንቱም ሰባት ናብ ዓድዋ ኣይትኺዱ* | *"እናንት ሰዎች ወደ ዓድዋ እንዳትሄዱ* |
| *ብእሳተ ገሞራ ከይትነዱ* | *በእሳተ ገሞራ እንዳትነዱ* |
| *ኣባ በዝብዝ ካሳ ቆራፅ እዩ ኸብዱ"* | *ኣባ በዝብዝ ካሳ ቆራጥ ነው ሆዱ"* |

(www.africanidea.org/atse_yohannes.pdf)

ነገር ግን ሁለቱ ባላጋራዎች ሲዘጋጁ ከርመው በ1863 ዓ.ም ካሳን ለማስገበር ከከተማቸው ተነስተው የተከዜን ወንዝ ተሻግረው ወደ ዓድዋ ጉዞ ጀመሩ፤ ውጊያውም በሓምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን በጣም ኣጭር በሆነ ጊዜ (ዘውዴ ገ/ሥላሴ ጦርነቱ ኣራት ሰዓት ብቻ እንደፈጀ ይገልጻሉ) በደጃች ካሳ ኣሸናፊነት ተደመደመ። ከጦርነቱ በኋላ እቴጌ ድንቅነሽ በሚከተለው ግጥም ቆዝመዋል፤

*"ተናግሬ ነበር እኔስ ኣስቀድሜ*

*ኣሁን ምን እላለሁ በሃዘን ላይ ቆሜ*

*ተሻረው ባሌ ነው ተሿሚው ወንድሜ*

*ከእንግዲህስ ወዲያ ኣልመኝም ዕድሜ"*

ኣንጋፋ ታሪክ ፀሓፊው ተክለጻድቅ መኩሪያ (ዐፄ ዮሓንስ እና የኢትዮጵያ ኣንድነት፣ (1982) በሚለው መፅሓፋቸው ላይ) "ዐፄ ተክለጊርጊስን ካሸነፉ በኋላ፣ በትግራይ፣ በበጌምድር፣ በጎጃምም፣

በሸዋና በወሎም ሊቋቋማቸው የቻለ ኃይል ስላልነበረ ወደ ንጉሠ-ነገሥትነት የሚያደርሰው መንገድ ለሳቸው ተከፈተ" ይላሉ።

## የአፄ ዮሓንስ ሥርዓተ-ንግስ

ለሥርዓተ-ንግሱ የሚያስፈልገው ማናቸውንም ዝግጅት ካደረጉ በኋላ በጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ስመ-መንግስታቸው "ዮሓንስ አራተኛ" ተብሎ በጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው በሥርዓተ መንግስት ነገሡ። በዚሁ ንግስ ምክንያት 3 ቀን በዓል ሆኖ ለግብር 4,000 ሠንጋ ታርዶ 50 ጉንዶ ማር የፈጀ 150,000 ገንቦ ጠጅ ቀርቦ በደስታ ሲበላ ሲጠጣ እንደሰነበተ ሙሴ ጂ. ዲወ በዝርዝር ጽፎ አትሞታል።

"ነገር ግን ከነገሡ ዠምሮ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ከሁሉ የበለጠ ላፄ ዮሓንስ ዋና ባላንጣ ሆነው የተገኙት የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ናቸው" ይላሉ ተክለፃድቅ መኩሪያ እላይ በተጠቀሰው መፅሓፋቸው ላይ፤

## አፄ ዮሓንስና ኃይማኖት

አፄ ዮሓንስ፥ ጥብቅ ሃይማኖተኛ፣ ከፍተኛ የሞራል ልዕልና የያዙና ቅን አሳቢ እንደነበሩ ታሪካቸውን የጻፉ የተለያዩ ፀሓፍት ዘግበውታል፤ በተዋህዶ ኃይማኖት ተነስቶ የነበረውን ሃይማኖታዊ ክርክር ለመፍታት የቦሩ ሜዳ ጉባኤ እየተባለ የሚጠራውን ስብሰባ በመጥራት፣ ልዩነቶቹን በወሳኝ መልኩ እንዲፈቱ አድርገዋል።

ከምኒልክ የበለጠ ዮሓንስ ለኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀናዒ በመሆን በግዛታቸው የነበሩትን የካቶሊኮቹን ስብከት ሲቃወሙ በተለይ ዐፄ ተክለጊዮርጊስ የተሸነፉ ዕለት ሰነድ ሲመረመር የካቶሊኮች መሪ ሞንሲኞር ዠን ቱቪዬ "ከካሳ ጋር በሚያደርጉት ጦርነት፣ የጦር መሣሪያ በማቀበል እንረዳዎታለን" የሚል ለዐፄ ተክለጊዮርጊስ የተጻፈ ደብዳቤ ስለተገኘ፣ ቀድሞውንም የማይወዱቸውን ካቶሊኮች ከዚህ ጊዜ ዠምሮ ንብረታቸውን በመውረስ አጉላሏቸው፤ በርሳቸው አንጻር ምኒልክ በካቶሊኮቹ በነ አባ ማስያስ በኩል ከኢጣልያና ከፈረንሳይ መንግሥታት ባላንጣዬን የምቋቋምበት የጦር መሣሪያ አገኛለሁ በሚል ተስፋ ካቶሊኮችን ተንከባከቧቸው።

ምኒልክ በተዋህዶ ሃይማኖት በኩል ያላቸው ዝና እየተበላሸ ሲሄድ በሌላው አንጻር በፈረንሳይና በኢጣልያ አገር ግን ዮሓንስ እምቢ ባይ፣ የካቶሊክ እና የእስላም ጠላት፣ አሳበ ግትር (fanatic) እየተባለሉ ሲነቀፉ፥ ምኒልክ ደግሞ ታጋሽ፣ የሃይማኖት ነፃነት ሰጭ፣ አገሩን ለማሰልጠን መልካም ፈቃድ ያለው ተብለው ተወድሰዋል።

## አፄ ዮሓንስና ጦርነት

የዱሮ ንጉሦች ጦርነትና ውጊያዎችን እንደ ጨዋታ የሚያዩት ሲሆን በአንጻሩ አፄ ዮሓንስ፣ የሰው ሕይወት በከንቱ እንዲጠፋ ፈጽሞ አይፈቅዱም ነበር፤ ወደ ጦርነት ከመግባታቸው በፊት ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ መንገዶችን በሙሉ አሟጠው በመጠቀም ቅራኔዎችን ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፤

እነዚህ ሁሉ ተደርገው ሳይቻል ሲቀር ግን በሙሉ ልብ ነው ወደ ጦርነቱ የሚገቡት፤ ወደ ጦርነት ሲገቡም ቆፍጣና ወታደርና ብልህ የጦር መሪ ናቸው።

አፄ ዮሓንስ እ.ኤ.አ ከ 1875-1889 ዓ.ም ድረስ ከውጭ ወራሪዎች የተሰነዘሩ ስምንት ጦርነቶችን ለመጋፈጥ ተገደዋል፤ (ገ/ኪዳን ደስታ፣ የትግራይ ሕዝብና የትምክህተኞች ሴራ፣ 1998 ዓ.ም፣ ገፅ 4)

ንጉሠ-ነገሥት ከሆኑ በኋላ የመጀመሪያው የውጭ ወረራ የተቃጣባቸው፣ ከግብፁ ከዲቭ እስማኤል ነው፤ ግብፆች ይዞታቸውን ለቀው ወደ ደጋው የኤርትራ ክፍል በተሳቡ ጊዜ፣ በመጀመሪያ ለግብፁ መንግሥት መሪ "አንተም ከአባቶችህ አትበልጥም፣ እኔም ከአባቶቼ አላንስምና፣ በየይዞታችን ሆነን በሰላማዊ ግንኙነት እንቀጥል" ቢሉት በጀ የሚል ስላልሆነ፣ ቀጥሎም ለአውሮፓውያኑ መንግሥታት እንዲያገላግሏቸው ደብዳቤ ልከዋል፤ ሆኖም አውሮፓውያኑም የተዛባ መረጃ ስለደረሳቸው ይሁን ወይም ለገዛ ተንኰላቸው ሲሉ ለጉዳዩ መፍትሔ ሊሰጡ አልቻሉም።

የግብፁ ጦር መሪ አፄ ዮሓንስን ለማታለል ደብዳቤ ቢልክም ንጉሠ-ነገሥቱ ግን የሚሰልሉ ሰዎች ልከው ሁኔታውን ተከታትለዋል፤ እነዚህ ሰዎች የግብፆችን የፈረሶቻቸው ብዛታቸውን ጽናታቸውን ገለጡላቸው" ካለ በኋላ፣ ንጉሠ-ነገሥቱ አፄ ዮሃንስ "ኃይለኛ በሰራዊቱ ብዛት አይድንም፥ ፈረሰኛም በፈረሱ ጽናት አያመልጥም" ብለው፣ ዐይናቸውን ወደ ሰማይ ሰቅለው "ሕዝብህን ከጥፋት አድን፣ ርስትህንም ባርካት፣ ለኛ ለአገልጋዮችህ የማሸነፍ ኃይል ስጠን" ብለው ጸልየው ወደ ጦርነቱ ጉዞ መገ'መራቸውን ያመለክታል፤ (Bairu Tafla(ed.) A Chronicle of Emperor Yohannes IV, F.140)

በምጥዋ የፈረንሳይ ቆንሲል ደርላዜክ በዚሁ ጊዜ የፈረንሳይ መንግሥት መልዕክት ይዞ ወደ ዓድዋ መጥቶ ከንጉሠ-ነገሥቱ ጋር ሆኖ ሁሉንም ይመለከት ስለነበረ፣ ስለ ጉዞውና ስለ ጦርነቱ አገ'ማመር በበኩሉ እንዲህ ይላል፤ "ዮሓንስ በ 2 ሕዳር 1875 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ቤተ መንግሥታቸውን ከጧቱ በአምስት ሰዓት በለቀቁ ጊዜ ታላቅ የመሬት መናወጥ ተቀስቅሶ ከሰሎዳ ተራራ ላይ የተፈነቃቀለው የደንጊያ ናዳ እየተንከባለለ ከንጉሡ እግር ሲደርስ በግንባራቸው ተደፍተው ለሰራዊት አምላክ ሰግደው ቀና ካሉ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሰራዊታቸው መልሰው "ይህ አስደንጋጭ ምልክት አረመኔዎቹ (ግብፆች) በጥንታዊቱ ኢትዮጵያ ተቀብረው ለመቅረታቸው አምላክ የሰጠው ምልክት ነው" ብለው ከተናገሩ በኋላ ከዓድዋ ተነስተው ወደ ጦርነቱ ቦታ ጉዞኣቸውን ቀጥለዋል፤...." ((J.de Coursac, Le Regne de Yohannes IV, pp306)

የመጀመሪያው የጉንደት ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተደመደመ። ግብፆች ግን በኢትዮጵያውያን መሸነፍ ውርደት አድርገው ስለቆጠሩት፣ አፄ ዮሓንስን በመውጋት 'በደንብ ትምህርት ሰጥቶ ለመቅጣት' የሚችል እና ያለፈውን መሸነፍ ተቀብሎ የግብፅን የተዋጊነት ዝና የሚመልስ በጣም ከፍ ያለ የጦር ድርጅት በትጋት አካሂዶ በሁለተኛው ወረራ እንደገና ኣሥመራ አጠገብ ወደሚገኘው ጉራዕ ወደተባለው ቦታ ተንቀሳቀሰ።

በዚህን ጊዜ ሰላም እንፍጠር እያሉ በደብዳቤ ለግብፁ ከዲቭ እስማኤል ያሳሰቡት ነገር ምንም ዓይነት ውጤት ሳያስገኝ መቅረቱንና በዚህ ፈንታ የግብፅ ጦር ከቀድሞው በበለጠ ተዘጋጅቶ መምጣቱን የተረዱት አፄ ዮሓንስ "የአጋርና የእስማኤል ልጆች፥ ኢስማኤላውያን፣ ሞዓባውያን፣ ኤዶማውያን የተቀደሰችው አገራችንን በመውረር ሕዝባችንን ባሪያ አድርገው ለመግዛት መጥተውብናል፤ ሁላችሁም ስለ አገራችሁና ስለ ሃይማኖታችሁ ጠላትን መመከት አለባችሁ፤" በሚል አዋጅ ሰራዊታቸውን ከቀሰቀሱት በኋላ፣ ጠላትን ለመውጋት ዳግም ተንቀሳቀሱ። (H. Erlich, A political Biography of Ras Alua, pp.60-61)

በሁለተኛው ጦርነት የግብፅ ጦር በከፍተኛ ሁኔታ ተዋግቶ በከፍተኛ ሁኔታ ተደመሰሰ፤ በሁለተኛው ጦርነት መሸነፍ ጎን በዋናው የግዛት አቀንቃኝ በነበረው በወርነር ሙንሲንጀር ሞት ሳቢያ ከካይሮ እስከ ዛንዚባር፣ ወይም ከሜዲቴራንያ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ሊዘረጋ ታስቦ የነበረው ሰፊው የእስማኤል የቄሳር ግዛት ምኞት ዓላማ ከሸፈ። ግብፆች፣ በሁለቱም ጦርነት ከ 12-13,000 ሰው ስለ ሞተባቸው፣ 39 መድፍ፣ 15,000 ጠበንጃ፣ 40,000 በቅሎና ግመል ስለተማረኩባቸው፥ ከፍተኛ ወታደራዊ፣ የኢኮኖሚና የሞራል ውድቀት ደርሶባቸዋል።

አፄ ዮሓንስ ሁለት ጊዜ በግብፆች ላይ ያገኙት ድል አድራጊነት በወታደራዊ መስክ ዝናቸው በያለበት እያደመቀው ሄዷል፤ ባለቅኔውም እንዲህ ሲል አወድሷቸዋል፤

*"ከላይ የወረደው ከጽዮን መቅደስ*

*ባባቱ ሚካኤል* በናቱ ስላሰ*

*አጨደው ከመረው ያን ያሕዛብ ገብስ*

*ወቃው ደበደበው ሰጠው ለነፋስ*

*ዐሊሙ ነፍጠኛ ሃፀይ ዮሓንስ"*

(ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ - ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለሥላሴ)
( *ባለቅኔው *'ባባቱ ሚካኤል'*ሲል፣ ከስሑል ሚካኤል የዘር ሃረግ የመጡ መሆኑን ለማመልከት የፈለገ ይመስላል)

አፄ ዮሓንስ ሁሉንም በኢትዮጵያ ላይ የተቃጡ ወረራዎችን በብቃትና በጀግንነት መክተዋል፤ በመጨረሻም 'ቅድስት' ለሚሏዋት አገራቸው በጦር ሜዳ ከጠላት ሲከላከሉላት፣ በሙተማ ላይ ወድቀዋል፤ በወቅቱ የነበረውን የሕዝብ ስሜት በሚወክል መልኩም፣ ገጣሚው ፍፃሜያቸውን በሚከተለው መልክ ተቀኝቶታል፤

*"በጎንደር መተኮስ*

*በደንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሓንስ*

*ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ፣*

*እንዳያምረው ብሎ ድሃ ወዳጁን*

*መተማ አፈሰሰው ዮሓንስ ጠጁን፣*

*የጕንደር ኃይማኖት ቆማ ስታለቅስ*

*አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሓንስ።"*

(ባለቅኔው *'ዳግማይ ዮሓንስ'*ሲል የመጽሓፍ ቅዱሱ መጥምቁ ዮሓንስ በሄሮድስ አንገቱ መቀረጡ፣ እሱ የመጀመሪያ ሆኖ አፄ ዮሓንስ የመፅሓፍ ቅዱስ አማኝ ሃይማኖተኛ ሆነው አንገታቸው የተቀረጠ ሁለተኛው ሰው መሆናቸውን ለማመልከት የፈለገ ይመስላል፤)

## <u>ኣፄ ዮሓንስና የኣገር ግንባታ ሂደት</u>

ኣፄ ዮሓንስ ከዕድገታቸውና ከሥርዓተ-ንግሳቸው ጀምሮ የአደባባይ ሰው ናቸው፤ ሃይማኖታቸው፣ ንግግራቸው፣ ትዕዛዛቸው፣ ቆራጥነታቸው፣ ተግባራቸውና ውሳኔዎቻቸው ሁሉ ስርዓታዊ (formal) ናቸው፤ በጓዳና በድብቅ የሚያከናውኑት ነገር አልነበረም፤ ጠላትን በጦርነት ከመግጠማቸው በፊት እንኳን "የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ" በማለት የዓለም ሽማግሌዎችን (በወቅቱ የሰለጠኑ የአውሮፓ መንግሥታትን) ይማጠናሉ፤ በጠላት ጎራ የተሰለፈውን ኃይልም ይለምናሉ፤ ይኼ ሁሉ አልሆን ብሎ ወደ ጦርነት የሚገባ ከሆነ ግን በሙሉ ወኔና ቆራጥነት ነው የሚገቡት፤ እነዚህ ኣገርን ከመገንባት ኣኳያ ወሳኝ ግብኣቶች ናቸው፤ የኣገሩን ሰው በመቅረጽ ረገድ ጠቃሚ እሴቶች ናቸው።

በኣገሪቱ በአራቱም ኣቅጣጫዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ እየተወረወሩ ኣስተዳደር ኣቁመዋል፣ ዐመፀኛን በመቅጣት ፍትሕ ኣፅንተዋል፣ ድንበር የደፈረ ጠላትንም በጦር ሜዳ ቀጥተው መልሰዋል፤ ሕዝቡም ኣገሩን እንዲወድ፣ በቃልም በግብርም መርተዋል፤ በዚሁ ሥራቸውም ለኣገሪቱ የወደፊት ጉዞ ጠንካራ መሠረት ኣኑረዋል።

ኣፄ ዮሓንስ፣ የጦርነት ኣዋጅ ሲያውጁ ሕዝቡ የኣገሩ ባለቤት መሆኑን በሚገልጽ ድምፀትና እንድምታ ነው መልዕክቱን የሚገልጹት፤ ኣገሩም በሙሉ ልቡ ይከተላቸው ነበር።

ለኣብነት፣ ጣልያኖችን ለመውጋት ሲነሱ፥ በነጋሪት ያሳወጁት ኣዋጅ የሚከተለውን ይመስላል፤

*"የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ፣ ልብ ኣድርገህ ተመልከት*

*ኢትዮጵያ የተባለችው፣ ኣንደኛ እናትህ ናት፤*

*ሁለተኛ ዘውድህ ናት፤ ሦስተኛ ሚስትህ ናት፤*

*ኣራተኛም ልጅህ ናት። ኣምስተኛም መቃብርህ ናት።*

*እንግዲህ፣ የእናት ፍቅር፣ የዘውድ ክብር፣*

*የሚስት ደግነት፣ የልጅ ደስታ፣ የመቃብር ከባድነት፣*

*እንደዚህ መሆኑን ኣውቀህ ተነሣ።"*

ይላል።

ይኼ ሁኔታ በዓድዋ ጦርነት ላይ ለታየው ሕዝባዊ ጀግንነት የራሱ የሆኑ እንድምታዎች ኣሉት። ኣንዳንድ ሰዎች፣ በምኒልክ ቤተ-መንግሥት ውስጥ የኣፄ ዮሓንስን መንፈስ ከወረሱት ሰዎች ውስጥ በዋናነት እቴጌ ጣይቱ ብጡል እንደሚገኙበት ያወሳሉ።

## <u>መንግሥታዊ ፍልስፍና</u>

ከብዙ ነገሥታት በተለየ፣ ኣፄ ዮሓንስ ኣገራቸውን ከራሳቸው ስልጣን በላይ የሚመለከቱ መሪ ነበሩ፤ ለእሳቸው፥ ኣገርና ወገን የመጨረሻ ከፍተኛዎቹ ልዕለ-እሴቶች ናቸው፤ ሁሉም ነገር የሚከናወነው፣ ሁሉም ሃሳብና ድርጊት የሚመነጨው እነዚህን ልዕለ-እሴቶች ለማገልገል ነው፤ የዚህ ማሳያ የሆኑ፣

*በዚህ ጽሑፍ በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ክንዋኔዎች የተገለጹ ቢሆንም፣ ኣንድ ኣብነት ለመጨመር ያክል፥ ንጉሠ-ነገሥቱ እንኳን ለመሬቷና ለሕዝቧ ይቅርና ለጥርኝ ኣፈሯም ይሳሱ እንደነበር የሚያሳየው፣ የውጭ ኣገር መልዕክተኞች ከደጋው የኤርትራ ኣካበባቢ ለመናፈሻ የሚሆን የተወሰነ ቦታ እንዲሰጣቸው በጠየቁ ጊዜ የሰጧቸው ምላሽ ጉልህ ምሳሌ ነው፤*

> *"…..እኔ የሃገሬ መሬት ለባዕድ ኣሳልፌ የመስጠት መብቱም ፍላጎቱም የለኝም፤ እንኳንና መሬት ጥርኝ ኣፈሯንም ኣልሰጥም"* ብለው መልዕክተኞቹ የጫማቸውን ትቢያ ኣራግፈው እንዲወጡ ኣድርገዋል።

*የመንግሥታቸው ኣካሄድ መርሆች፣ ታጋሽነት፣ መቻቻልና ይቅር ባይነት እና እንዲሁም ያለውን ሁኔታ ሳያደፈርሱ መጠበቅና ማሳደግ የሚሉ ነበሩ፤ ከሁሉም በላይ ግን 'ቅድስት' የሚሏት ኣገራቸውን ሰላም በውጭ ወራሪም ሆነ በውስጥ መቆራቆስ እንዲደፈርስ ኣይፈልጉም ነበር፤ የሰላም እጦት ምን እንደሚያስከትል ጠንቅቀው ያውቃሉና። ስለ ግላቸው ግዛታዊ ስልጣን ሳይሆን የሚጨነቁት ስለ ቅድስት ሃገራቸው ሰላምና ብልፅግና ነበር፤ ዋና ሃሳባቸው። ለምሳሌ ሥልጣናቸውን ከምኒልክና ከተክለሃይማኖት የተካፈሉበት መንገድ፣ የራሳቸውን ሥልጣን የሚቀንስ ነው፤ ነገር ግን የኢትዮጵያን ሰላምና ኣንድነት በማቀላጠፍ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፤ ኣሁን ፌዴራል ኣስተዳደር የምንለው ዓይነት ይመስላል፤ በየቦታው ያለውን የኣስተዳደር ሁኔታ ሳያደፈርሱ መጠበቅና ማበልፀግ የሚለውን መርሕ በመከተላቸው፣ በሕዝቡ ዘንድ ማለቂያ በሌለው መቀያየር ምክንያት ባለፉት መንግሥታት ይታይ የነበረውን ጥርጣሬና ፍራቻ በእጅጉ እንዲቀንስ ኣስችለዋል።*

*እንደሚታወቀው፣ ብዙ ነገስታት፣ ሁሉንም ነገር ከራሳቸው ስልጣን በታች ኣድርገው ነው የሚመለከቱት፤ ('ከራስ በላይ ንፋስ' እንዲሉ) ሁሉም ነገር ለሥልጣናቸው እስካላገለገለ ድረስ፣ ኣገርም ህዝብም ምንም ማለት ኣይደሉም፤ የፈረንሳዩ ንጉስ* 'Apres moi deluge' *('እኔ ከሞትኩ ሰርዶም ኣይብቀል' እንደማለት) ኣለ እንደተባለው ማለት ነው።*

*እንደ ሰው፣ ንጉሠ-ነገሥቱ ጥብቅ ኃይማኖተኛ፣ ባለ ልዑል የሞራል ደረጃ፣ ቸር፣ ጀግና እና ከፍተኛ በራስ መተማመን የነበራቸው ናቸው፤ በነዚህ ሁሉ ባሕሪያቶቻቸውና በጦርነት ድል ኣድርገው ለማረኳቸው ጠላቶቻቸውና ተቀናቃኞቻቸው ጭምር ያሳዩት በነበረው የይቅር ባይነት ኣቋም ምክንያት በተከታዮቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ኣድናቆትና ከበሬታን ኣስገኝቶላቸዋል።*

*እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ኣንዳንድ ጊዜ በውሳኔዎቻቸውና ተግባሮቻቸው፣ የዋህነት ያንፀባርቁ ነበር ይላሉ ኣንዳንድ ፀሓፊዎች። የተቀናቃኞቻቸው መሰሪ ባህርያትም እንዳይገነዘቡ ይኼ ባህርያቸው ጋርዷቸው ነበር ይላሉ፤ ዞሮ ዞሮ ግን ኣንድ ሰው በኣንድ ጊዜ የዋህም መሰሪም ሊሆን ስለማይችል፣ በራሳቸው ባሕርይ ኣማካኝነት ላከናወኑት ተግባርና በባሕርያቸው ክፍተት ምክንያት ለደረሰባቸው ውድቀት ታሪክ በዚሁ መልኩ ሲያስታውሳቸው ይኖራል።*

## ኣፄ ዮሓንስና ራስ ኣሉላ

*ራስ ኣሉላ የኣፄ ዮሓንስ ስመ-ገናና ጀኔራል ናቸው፤ እንደሚታወቀው በመንግሥታዊ የሥልጣን ተዋረድ መሠረት ንጉሠ-ነገሥቱ የኣገሪቱ የመጨረሻ ከፍተኛው መሪና ባለ ሙሉ ሉዓላዊ ስልጣን ያለው ሰው ነው፤ ታድያ ምን በሚሉት 'ሳይንስ' ነው ኣንዳንድ ፀሓፊዎች ንጉሠ-ነገሥቱን ዝቅ ለማድረግ እየሞከሩ የበታቻቸውን (ኣሽከራቸውን) ነጥለው ለማወደስ የሚሞክሩት? ይህቺ ኣነጋገር ሽታዋ ደስ ኣይልም፤ የሆነ 'የገለማ' ነገር ኣላት።*

ስለዚህ፣ ንጉሠ-ነገሥት ኣፄ ዮሓንስ በዘመነ-መንግሥታቸው ለተገኙ ሁሉም የሃገሪቱ ድሎች ዋነኛው ሰው መሆናቸው ማስረገጥ ኣስፈላጊ ነው።

ይኼ ሲባል፣ የራስ ኣሉላን ሚና ማሳነስ ማለት ኣይደለም፤ ነገር ግን ሁሉም ነገር በሚዛኑ ሲቀመጥ ትክክል ይሆናል ለማለት ነው።

## መደምደሚያ

የታላቁ ንጉሠ-ነገሥት ኣፄ ዮሓንስን ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ፣ የኣክራሪዎችን የተወለጋገደ ትረካ ለመመከት ያክል ለመፃፍ ተሞክሯል፤ ኣፄ ዮሓንስ የኢትዮጵያ ሙሉ ንጉሠ-ነገሥት የነበሩና እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ለቅድስት ኣገራቸው የተጉ፣ የደከሙ፣ ላይ ታች የባተሉ፣ ለትውልድም የጀግንነት ውርስ ያወረሱ ታላቅ መሪ ናቸው።

ስለዚህ፣ የኣገራችን ኣክራሪዎች፣ ኣንድ ወንዝ በማያሻግረው ጭፍን ቀበሌያዊ ኣስተሳሰባቸው እየተመሩ፥ የመሪነት ሳይሆን የ 'ገዥነት' ስልጣን ለነሱ ብቻ የተሰጠ 'ፀጋ' እንደሆነ እየተዘባነኑ በእንድምታ እየገለጹ የኣገርን ያክል ታሪክ ባይበርዙና ባይከልሱ መልካም ነው እላለሁ። 'ሲተኩስ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ' የበሉባትና የበሉኣት ሃገር ያስረከቧቸው ጀግና ንጉሠ-ነገሥት ለማቅለል መሞከራቸውም 'በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ' ያሰኛል።

ባጠቃላይ ከታሪካችንና ከነገሥታቱ መማር ያለብን ጥሩውን ለመውሰድና ለማበልፀግ፥ መጥፎውን ደግሞ ለመቀነስና ለመገደብ መሆን ኣለበት፤ የሚል እይታ ኣለኝ።

ለምሳሌ ከኣፄ ቴዎድሮስ፣ ኣርቆ ኣሳቢነታቸውንና ጥንካሬያቸውን መውሰድ ሲገባን፣ ጭካኔያቸውን ግን መገደብ ኣለብን፤ የጭካኔ ነገር ሲነሳ ኣንድ ማሳያ ባስቀምጥ እወዳለሁ፤

> "*.........የተማረከውን የወሎ ሰው እያስያዙ ሁለት እግሩና ሁለት እጁን እየቆረጡ በኣንገቱ ላይ እያሰሩ ወደ ቤቱ ሰደዱት፤ የወሎ ሰው እነዚያ የተቆረጡትን ባየ ጊዜ እጅግ ደነገጠ። ኣጥብቆ ተሸበረ። ደግሞ የወሎ ሰው እንዲህ ኣለ፤*
>
> *'ማጉረስስ ምሽቱ ታጉርሰው*
>
> *ቂጡን እንዴት ያብሰው፤'*
>
> *ኣለ።"* (ተስፋዬ ኣካሉ ኣበበ፣ ኣጤ ቴዎድሮስ፣ 2004 ዓ.ም፣ ገጽ 144)

ከኣፄ ዮሓንስ ጀግንነት፣ የወገን የእናት ሃገር ፍቅር መውረስ ሲገባን፥ የዲፕሎማሲ ክፍተትን ደግሞ ማሻሻል ኣለብን።

ከኣፄ ምኒልክ፣ የኣዲስ ቴክኖሎጂ ተቀባይነትን መውሰድ ሲገባን፥ ድብቅነትን፣ ሴረኝነትንና፣ ሸፍጥን ደግሞ መገደብ ኣለብን፤ ኣፄ ምኒልክ በወቅቱ በቤተ መንግሥታቸው ኣካባቢ ድብቅነት የነገሠ በመሆኑ ሲሞቱ እንኳን በግልጽ ለሕዝቡ ኣልተነገረም፤ ህዝቡም በወጉ ኣልቅሶ ሊቀብራቸው ኣልታደሉም፤

*እንዲያውም ድብቅነቱ በፈጠረው የሃሜት ባህል፣ ስለ ኣሟሟታቸው ራሱ ኣንዴ በኣባለዘር (ቂጥኝ) ኣንዴ ደግሞ በቁምጥና ነው የሞቱት እያለ ህዝቡ ሲያንሾካሽክ እንደነበረ ይነገራል።*

*በነገራችን ላይ፣ ከላይ ይገደቡ የተባሉት ነገሮች ኣንዳንድ ሰዎች እንደ ዋነኛ እሴቶቻቸው ኣድርገው እንደሚወስዱዋቸው ይታወቃል፤ በኣገር ደረጃ ግን ይኼ መሆን የለበትም፤ ኣለዚያ፣ ልጁን ትቶ የእንግዴ ልጁን እንደመውሰድ ሊሆን ነው።*

*ይኼን ጽሑፍ፣ የጎንደር ከተማ ልዑካን በ 2003 ዓ.ም የከተሞች ቀን በዓል ለማክበር፣ ወደ መቀለ ከተማ በመጡ ጊዜ ለከተማው ኣስተዳደር በስጦታ መልክ ባስረከቡትና ኣሁን በኣፄ ዮሓንስ ቤተ-መንግሥት በር ላይ ተተክሎ በሚገኘው ቅስት ላይ በተፃፈው ፅሑፍ ባጠቃልል እወዳለሁ፦*

**ይህን ታላቅ ቤተመንግስት የገነቡት ታላቅ መሪ ታላቋን ኢትዮጵያ ለ17 ዓመት ከ52 ቀን ያህል በታላቅ ወኔና ሀገራዊ ፍቅር የመሩት አፄ ዮሐንስ 4ኛ ናቸው።**

**አፄ ዮሐንስ 4ኛ ከወርሃ ጥር 1864 እስከ ወርሃ መጋቢት 1881 ኢትዮጵያን በመሩበት ወቅት ይህች ሀገር ከተለያዩ ወራሪዎች የሚቃጣባትን የወረራ ሙከራ የመከቱ ንጉስ ሲሆኑ በመጨረሻም ከጎንደር ከተማ በ220 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው መተማ ዮሐንስ ስለሀገራቸው ዳር ድንበርና አንድነት ሲሉ በወርሃ መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም መስዋዕት ሆነዋል። እኒህን ህያውና ጀግና መሪ ታሪክ መቼም አይረሳቸውም።**

***ጎንደር ከተማ አስተዳደር***